# አጀንዳ መምራት ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ

በታምራት ደጀኔ

ታህሳስ 2013 ዓ.ም

# የወረቀቱ ይዘት

ክፍል 1፣ የተግባቦት ምንነት፣ መሰረታዊ ባህርያት

ክፍል 2  የተግባቦት ሂደት

ክፍል 3፣ አጀንዳ ቀረጻ ምንነትና ጠቀሜታ

ክፍል  4፣ የአጀንዳ አመራር፣ ግንባታና ኦንላይን አጀንዳ ቀረጻ ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ

·ክፍል 5  ማጠቃለያ

# መነሻ ጥያቄ

1. በአሁኑ ወቅት የአብዛኛውን የአገራችን ህዝብ ቀልብ የሚስብ አንገብጋቢ ጉዳይ  ወይም ኩነት ምንድን ነው

2. መገናኛ ብዙሃን አጀንዳ መምራት/መቅረጽ ይችላሉ  ወይ  ?  እንዴት?

3.  የኮሙኒኬሽን ባለመያዎች አጀንዳ መምራት/መቅረፅ ይችላሉን??

# ተግባቦት ምንነት፣ መሰረታውያን፣ባህርያት

## ተግባቦት

- መረጃ የማድረስ ፣ ሃሳቦች እና አመለካከቶችን መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ለበርካታ ተደራሲያን (ብዙሃን ህዝብ) የማሰራጨት አላማ ያለው የስራ ሂደት ነው

Mass Communication: The process of delivering information,ideas,and attitudes to a seizable and diversified audience through the use of media developed for that purpose.

# ተግባቦት በአመለካከትና በዝንባሌ ላይ የሚያሳድራቸው ተጽእኖዎች

- በ1770ዎቹ ቶማስ ፔይን በአሜሪካ አብዮት ወቅት ‘Common sense’ በሚል ያሳትማቸው የነበሩ በራሪ ዕሁፎች ቅኝ ተገዝዎቹን የነጻነት መግለጫ ሰነዱን እንዲደግፉና ለለውጥ እንዲነሳሱ አድርጓል።
- የህዝብ አስተያየት ከፍተኛ ማህበራዊ ተጽእኖ እንዳለው ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሁፍ ያዋቀረው የሃርቫርድ መምህሩና ፕሮፓጋንዲስቱ ቫልተር ሊትማን ነው።
- በተመሳሳይ ተቋም የህግ ፕሮፌሰር የሆኑት ሃሮልድ ላስዌል ከሙኒኬሽን መልእክተ በመቅረጽ የሰዎችን አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ መለወጥ እንደሚቻል (Hypodermic effect) እና ለመልእክት አመንጪው መልእክቱ እንደ ነሀስ አረር (Silver Bullet) ኢላማውን መምታት የሚያስችል እንደሆነ በ1930ዎቹ መጀመሪያ ገልጸዋል።
-

# የተግባቦት ተጽእኖ...

- **በብዙሃኑን ተደራሲያን ተቀባይነት ያገኙ ሃሳቦችና እምነቶች (Conventional Wisdom)፦**
  - በ1940ዎቹ Orson Wells እና CBS ሬዲዮ ከማርስ ያልታወቁ አካላት ኒውጀርሲ ፕሪንስተን አካከቢዎች ወርደው ወረራ አድርገዋል የሚል አስደንጋጭ ዜና ለቀቁ።
  - በርካታ የገጠር ከተሞች መደበኛ ሬዲዮ ጣቢያዎች ዜናውን ተቀብለው በማስተጋባታቸው ፣ ዜናውን ማስተባበያ ማለትም የH.G.Wells የተባለ ደረሲ War of the Worlds ልቦለድ የተቀዳ የሃሰት ዜና እንደሆነ ሪፖርት ለማዳመጥም ጆሮ ሳይሰጡ ነዋሪዎቹ አካባቢያቸውን መልቀቅ ጀመሩ።
  - መገናኛ ብዘሀኑን በምርጫ ወቅት ህዝቡ መሪውን መምረጥ ሲያቅተው /ሲቸገር ሬዲዮና ጋዜጦች መሪ የማቅረብ ሚናም ተጫውቶ ያውቃል።
  - በ1940ዎቹ Wendel Wilkie ለሪፐብሊካን ፓርቲ እጩ መሪ ሆኖ እንዲቀርብ እድረጓል-We want Willkie!

# የተግባቦት ተጽእኖ...


- የWater Gate ቅሌት በኮሙኒኬሽን ሳይንስ በተደጋጋሚ በምሳሌነት ከሚጠቀሱ የመገናኛ ብዙሃን ተጽእኖ የመፍጠር ብቃት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ነው።
- ፕሬዜዳንት ኒክሰንድጋሚ መመረጥ ቢችሉም የተቀናቃኝቸውነ የዴሞክራቲክ ፓርቲ ጽ/ቤት ሰብረው በመዘረፋቸው ዘመናቸውን ሳያጠናቅቁ ከስልጣን አውርዷል።

https://www.youtube.com/watch?v=IHnmriyXYeg


- ክስተቱን መነሻ በማድረግ ዋቂው የኮሙኒኬሽን ተመራማሪ የሆነው ዊልበር ሽራም ኮሙኒኬሽን ሰዎች ከዚህ በፊት ከሚያሳዩት ባህርይ በተለየ ሁኔታ ስሜታቸውን ሊያነሳሳ፣ የያዙትንም ልማድ በማስተው ከፍተኛ ተጽእኖ ማድረግ ይችላል የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ችሏል።
- በ1980ዎቹ የተግባቦት ሳይንስ ዋነኛ ትኩረት አጀንዳ ቀረጻ ሆነ። በዚህም መገናኛ ብዙሃን ከበርካታ ሃሳቦችን እና ኩነቶችን መካከል መልእክቶችን/ይዘቶችን በመምረጥ የህዝቡን (የተደራሲያንን) ቀልብ መያዝና ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተደረሰበት።

# የኮሙኒኬሽን (ተግባቦት)አይነቶች


የእርስበእርስ ግንኙነት




የቡድን ተግባቦት




የብዙሃን ተግባቦት



# ክፍል 2፤ የተግባቦት ሂደት

## የተግባቦት ዋናዋና ገጽታዎች፣

1. የኮሙኒኬሽን ባለሙያ (መልእክት አመንጪ /ኢንኮደር)
2. መልእክት(ኮድ፣ ምልክቶች)
3. መልእክት ማስተላለፊያ መንገዶች (ቻናል)
4. ተደራሽ (መልእክት ተቀባይ/ዲኮደር)
5. ግብረመልስ(ፊድባክ ኢፌክት)

# የተግባቦት ሂደት

- መልእክት(ኮድ)፣ ቋንቋ፣ ቪዥዋል ምልክቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣
- አንድ መልእክት በመገናኛ ብዙሃን ከመሰራጨቱ በፊት በርካታ ሂደቶችን ያልፋል፣
  - በር ጠባቂዎች ፣- (የዜናና የፕሮግራም አርታኢዎች)
  - ተቆጣጠሪዎች - የህዝብ ተጽእኖ ፈጣሪዎች(ፕሬዝር ግሩፕስ)፣ የመንግስት ቆጣጣሪዎች፣ ማስታወቂያ አስነጋሪዎች፣ ሽማቾች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ህግ አውጭዎች የመገናኛ ብዙሃን የሚየስታለለፉትን ይዘት እና አፈጻጸማቸው ላይ ተጽእኖ የሚያደርስ ሚና አላቸው።
  - ፊልተርስ( Frame of reference ) ( መልእክቱን ማመዛዘን/ማጣራት፣ ከልምድ፣ ከእሴት፣ ከባህል፣ ከሚደግፈው/ከሚያወግዘው ቡድን በመነሳት፣

# የተግባቦት ሂደት

- **የተደራሲው መልእክ የማጣራት  ሂደት** የተግባቦት ውጤታማነትን ይወስናል። ምክንያቱም መልእክት ተቀባዩ የተሰራጨውን መልእክትሊቀበለው ወይም  ላይቀበለው ይችላል።
- **የተደራሲው መልእክት  ያለመቀበል /አለመስማመት(ዲሶንንስ) ችግር** ሌላው የተግባቦት ሂደትን የሚያደናቅፍ ነው። ይህ ችግር የሚፈጠረው የሚተላለፈው መልእክት ከዚህ በፊት ይዞት ከቆየው ልምድ እና እምነት የተቃረነ ከሆነ ነው።
- **ስለዚህ ኮሙዩኒኬተሩ ከተደራሲው እምነትና ባህል ልምድ አንጻር** የተቃኘ መልእክት ማዘጋጀትና ማሰራጨት አለበት።

# የተግባቦት ሂደት

- ኮመዩኒኬተሮች የሚየጋጥማቸው ሌላው ችግር የመልእክት ማሰራጫ ዘዴዎች(ቻናልስ ኖይስ) ቴክኒካዊ ችግሮች ናቸው። የሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን መቆራረጥ፣ የጋዜጣ /መጽሄት ፊደላት ደቃቃነት ሊሆን ይችላል።
- የቻናል ችግር በጥቅሉ በመልእክት አመንጪው (ኮሙኒኬተሩ) እና በተደራሲያን መካከል የሚፈጠር ችግር (ዲስትራክሽን) ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።
- የሰለጠነ ኮሙኒከተር የቻናል ችግር ሲያጋጥመው መልእክቱ በትክክለኛና ተመራጭ ሚዲያ ማሰራጨት እና መልእክቱን በድግግሞሽ ማሰራጨት ይገባዋል።

# የተግባቦት ሂደት

- **የቃላት/የትርጉም መቃወስ ችግር (ሴማንቲክ ኖይዝ)፣** ኮሙኒከተሩ ትክክለኛ መልእክት በትክክልኛው ቻናል ቢያስትላልፍም ተደራሲው የተላለፈው መልእክት የተዛባ ትርጉም (ሚስአንደርስቱድ ) ከተደረገ የሚፈጠር ችግር ነው።
- ለምሳሌ ኮሙኒኬተሩ ተደራሲው ከሚያውቀው/ከለመደው ቃላት እና ስሞች ውጭ(ፍሬም ኦፍ ሪፈረንስ) ከተጠቀመና ኮሙኒኬተሩና ተደራሲው ቃላትና ስሞችን በተቃራኒ መልኩ የሚተረጉሟቸው ከሆነ
- ወይም የመዝገበ ቃላት ትርጉማቸው የተለየ ሆኖ ሲገኝ (ዴኖቴቲቭ) ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ በሌላ መልኩ የተፈረጀ ከሆነ (ኮኖቴቲቭ) ሴማንቲክ ኖይዝ ይፈጠራል።
- የሴማንቲክ ኖይዝ ችግር መቅረፍ የሚቻለው ኮሙኒኬተሩ ተደራሲው የለመዳቸውና በሚያውቃቸው ቃላትና ስምች መጠቀምና በትክክለኛ መዝገበቃላት ትርጉማቸው መልእክተ ማስተላለፍ ሲችል ነው።
- በእርግጥ አልፎአልፎ ከአውዱ በመነሳት ኮሙኒኬተሩ የሚጠቀማቸውን ቃላት ተደራሲው ሊገነዘብ ይችላል። ለምሳሌ ጁንታ፣

# መልእክት ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉ

## Selective Perception
## (Pro.Maxwell E.McCombs, Lee,B.Becker.)

- Selective Exsposure
- Selective Retention

# መልእክት ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉ

- ከሙኒኬተር ተደራሲያን መልእክት መርጦ ብቻ መቀበል(Selective Perception)፣ መልእክት ብቻ መከተል(Selective Exposure) ወይም መልእክት ብቻ መያዝ(Selective Retention) የመሳሰሉ የተደራሲያን ባህርያትን መረዳት አለበት።
- መልእክት መርጦ መቀበል ሲባል ከሙኒኬተሩ በዜና የሚሰራጩ መልእክቶች ከተደራሲያኑ ልምድ ጋር የሚጣጣምና የሚያውቀው የሚደግፈው ሃሳብ ከሆነ ፣ ከዚህ በተቃራኒ ከሚሰራጩ ዜናዎች ይልቅ በቀላሉ በተደራሲያኑ ቅብልነት የሚያገኙና ወደፊትም በቀላሉ ሊታወሱ የሚችሉ ናቸው።
- ፕሮፌሰር ሊን ፊትስንገር በአንድ ህክምና ማእከል የቀዶ ጥገና ክፍል ባደረጉት ጥናት ሃኪሙ በመገናኛ ብዙሃን ስለሲጋራ ጉዳት የሰጡት አጠቀላይ ትምህርት ሲጋራ አጫሾች በየቀኑ የሚጠቀሙትን ሲጋራ መጠን ሊቀንስ አልቻለም። ለዚህም ምክንያቱ አጫሾች በሲጋራ እና በሳንባ ካንሰር መካከል ያለው ግንኙነት የሚያሳምናቸው ሆኖ ባለመገኘቱ እንደሆነ ገልጸዋል።
- ይሁን እንጂ ጀርመናዊቷ ተመራማሪ ነዮል ኒውማን ባለንበት ዘመን መገናኛ ብዙሃን በሁሉም አካባቢ የሚገኝ እና በተደጋጋመ ሁኔታ መልእክተኞች የሚሰራጩ ከሆነ ማንም ከመገናኛ ብዙሃን ተጽእኖ ሊያመልጥ አይችልም ብላለች፣

## ክፍል ሶስት

# አጀንዳ ቀረጻ ምንነት፤ ጠቀሜታ፤

# 3.1. አጀንዳ ቀረጸ ምንነት፣ ጠቀሜታ

- የኮሙኒኬሽን ቀደምት ምሁር የሆነው ሃሮልድ ላስዌል የኮሙኒኬሽን መሰራዊ አለባውያን ብሎ ካስቀመጣቸው መካከል አንዱና ዋናው የአካባቢ ቅኝት ማድረግ ነው

1፣ **የአካባቢ ቅኝት ማድረግ**( surveillance of the environment)

2. **ለአካከቢ ለውጦች ማህበረሰቡን ማዘጋጀት** (correlation of the parts of the society in responding to the environment)

3 .**የማህበራዊ ቅርሶችን ለቀጣይ ትውልድ ጠብቆ ማስተላለፍ** (The transmission of the social heritage from one generation to the next)

# አጀንዳ ቀረጻ ምንነት፣ ጠቀሜታ

- አጀንዳ መምራት/ቀረጻ ተግባር ከመነሻው ከአርትኢያን ተግባርና ሃላፊነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የኮሙኒኬሽን ስራ ነው።
- የመገናኛ ብዙሃንን የአጠቃላይ የፖለቲካና ኦኮኖሚ እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነት ስርአቶች መካከል አንዱ ንኡስ ስርአት ስለሆነ መቆጣጠር ያስፈልጋል።
- ለበርካታ ዘመናት መረጃን መቆጣጠር ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያችለ እውቀት ለማስጨበጥ ሁነኛ መሳሪያ መሆኑ ታምኖበት ሲሰራበት ቆይቷል፣
- የመረጃ ፍሰቶችን የተቆጣጠሩ አካላት በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽእኖ መፍጠርና የበላይነት ማገኘት የሚያስችለ አቅም ይፈጥርላቸዋል።
- የአርትኢያን የዜና ታሪኮችን የመምረጥ ስራ ተራ የዜና ምርጫ ሳይሆን መረጃን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ግብአቶችንም የመቆጣጠር ጉዳይ ነው።

# አጀንዳ መምራት

- **አጀንዳ የመምራት /የመቅረጽ በማህበረሰ** /በአድማጭ ተመልካቾች አእምሮ ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆኑ መልእክቶችን የማስቀመጥና ተጽእኖ የማሳረፍ ሂደት ነው። የቫልተር ሊትማን ምክረ ሃሳብ እዚህ ጋር ይነሳል።
- የብዙሃን ተግባቦት ተመራማሪዎች የሆኑት **ማክስዌል ኢ. ማክኮምብ እን ዶናልድ ኤል ሾው** በ1972 ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ ምልከታ በመስጠት የአጀንዳ መምራት አለባውያንን አስቀምጠዋል።
- **የተለያዩ ኩነቶችን መገናኛ ብዙሃን ትኩረት ሰጥተው** መስራት አድማጭ ተመልካቹ አመለካከት ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ ያስችላል።
- የመገናኛ ብዙሃንምፋይዳ የግለሰቦች የስነአእምሮ ብቃት እንዲለወጥ (Cognitive change)፣ አስተሳሰባቸው እነዲሻሻል ማድረግ ነው ብለዋል።
- ተመራማሪዎቹ ለጥናታቸው መነሻ ያደረጉት የ1968ቱ የአሜሪካ ምርጫ ሲሆን ድምጻቸውን ለመስጠት ወይም ለመምረጥ ያልወሰኑት መራጮች በመገናኛ ብዙሃን በተቀረጸው አጀንዳ እና እነሱ ቁልፍ ጉዳይ/አጀንዳ ነው ብለው ባሰቡት ፍላጎት መካከል የተፈጠረው ልዩነት ከፍተኛ ዝምድና እንዳለው አረጋግጠዋል።
- **ነገር ግን መገናኛ ብዙሃን** ህዝቡ ቁልፍ ችግር/አጀንዳ ናቸው **ያሏቸውን ጉዳዮች ባያነሱም** በራሳቸው መንገድ የቀረጹት አጀንዳ በሂደት በህዝቡ ተቃባይነት የሚያገኝበትና የሚቀነቀንበት እድል እነዳለ ገልጸዋል።

# አጀንዳ አመራር/ቀረጻ ምንነትና መነሻ

- በ1976 የአሜሪካ ምርጫ ላይ በመመስረት የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ አመራር ጥናት ያደረጉት ፕሮፌሰር ዴቪድ ዌቨር ከቴሌቪዥን እና ከመራጮች አጀንዳ ይልቅ በህትመት መገናኛ ብዝሃን የተቀረጸው የምርጫ አጀንዳ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ተጽእኖ እንዳለው ገልጸዋል።
- .ማርሻል ማክልሃን የተባለ የኮሙዩኒኬሽን ተመራማሪ የመገናኛ ብዙሃኑ አይነት የሚተላለፈውን መልእክት ውጤታማነት ይወስናል የሚል አጨቃጫቂ ግን አዲስ ንድፈ ሃሳብ አመንጭተዋል።
- በዚህ ትኩስ እና ቀዝቃዛ ሚዲያ (Hot and Cool Media) ብለው በከፈሉት ንድፈሃሳብ በትኩስ ሚዲያ(ሲኒማ) የሚተላለፉ መልእክቶች ከነባሩ ሚዲያ(ቴሌቪዥን) አሳታፊ እና ጠቃሚ መልእክት ማስተላለፊያ አውታሮች ናቸው ብለዋል።

# አጀንዳ ቀረጻ ምንነትና መነሻ

- የመገናኛ ብዙሃን ጠቀሜታና ፍላጎት በማርካት ደረጃ ያለው ሚና (Uses and Gratificaions ) በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች ተደርገዋል።
- በዚህ ዘርፍ እስራኤላዊው የስነልቦና ባለሙያ ኢሊሁ ካዝ እና ፕሮፌሰር አሌክስ ኤደልስተን ይጠቀሳሉ።
- እንደኢሊሁ ካዝ አባባል መገናኛ ብዙሃን ከተደራሲያን ከሚያገኙት ጠቀሜታ ትኩረትት ከመስጠት ይልቅ ተደራሲያን ከመገናኛ ብዙሃን የሚያገኙትን ጠቀሜታ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል ብሏል።
- በዚህም ተደራሲያን የተለየያ የአካላዊና ውስጣዊ ፍላጎቶችን ለማርካት የተለያዩ መገናኛ ብዝሀኑን ሊከታተሉ እንደሚችሉ ገልጿል።
- ፕሮፌሰር ኤደልስተን በአሜሪካና ዩጎዝላቪያ ባደረጉት ጥናት ተደራሲያንመገናኛ ብዙሃንን የሚመርጡት ን በመረጃ ምንጫቸው ታማኝነት ሳይሆን በይዘታቸው (Content)፣ በጥልቅ ትንታኔያቸው (Breath of pereception)እና በቀላሉ ተደራሽ የሆኑትን (Availability)መገናኛ ብዙሃን ነው።
- በዚህ መሰረት ጋዜጦች በይዘታቸው፣ ቴሌቪዥን ስፋት ያለው ስሜት የሚይዝ ዘገባ ስለሚያስተናግድ እንዲሁም ሬዲዮ በቀላሉ የሚገኝ መሆኑ በሚል ይመረጣሉ በሚል ተፈርጀል።

# አጀንዳ ቀረጻ ምንነትና መነሻ

- ኒኦል ኒውማን የዝምታ አዙሪት (Spiral of Silence) ብላ በሰየመችው ጥናት በህዝቡ ውስጥ የተሰራጨው የህዝብ አስተያየት ግዝፈት ሰዎች የፖለቲካ አመለካከታቸውንና አቋማቸውን ሊለውጥ ይችላል፡
- ኒኦል እንዳለችው መገናኛ ብዙሃን የብዝሃኑን ህዝብ አስተያየት ተቀብለው የሚያስተጋቡ ከሆነ በሃሳብ ግብይቱ ብዙሃን ነን ብለው የሚያስቡቱ ሃሳባቸውን በነጻነት ለማስተጋባት ሲነሳሱ ውህዳን አፖለቲካ አቋም የያዙት ደግሞ ዝምታን ይመርጣሉ፣በነጻነት ለማውጣት አይበረታቱም።
- በቅርቡ የሚሰሩ ጥናቶች ከመደበኛው መገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ አጀንዳ መምራት ስራ የዜግነት ጋዜጠኝነት ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ መምጣቱ ነው።
- In Citizen Journalism, ordinary people create news stories on weblogs or personal websites about events they witness or issues that are on their minds.


# የአጀንዳ አመራር/ ቀረጻ አይነቶች

- አጀንዳ አመራር እጅግ አስፈላጊ የዜና ዝርዝር ታሪኮች መካከል ቅድሚያ የሚሰጠውን ( Priming) በመምረጥ እና አርታኢው በሚፈልገው መልኩ በማዘጋጀት(Framing) ሌሎች አጀንዳዎች ተጽእኖ እንዲያሳድር ማድረግ መቻል ነው።

- በዚህም ሶስት ዋነዋና የአጀንዳ አይነቶች ይገኛሉ።

  - የፖሊሲ አጀንዳ አመራር/ቀረጻ
  - የሚዲያ  አጀንዳ አመራር/ቀረጻ
  - የህዝብ አጀንዳ አመራር/ቀረጻ

# የአጀንዳ አመራር/ ቀረጻ አይነቶች...



# 3.2. የአጀንዳ ቀረጻ አይነቶች...

## 1ኛ፡ የፖሊሲ አጀንዳ አመራር /ቀረጻ

**የፖሊሲ አጀንዳ አመራር/ቀረጻ** ዜና ምን ያህል የህግ አውጭ አካሉ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር የሚያጠና ነው።

- ኮብ እና ኤልደር (Cobb and Elder) በ1972 እንዳሉት የፖሊሲ አጀንዳ የህዝብ አጀንዳ ይሆን ዘንድ አንዳች ኩነት የሚገፋው እና የህዝብ ድጋፍ ያለው ሊሆን ይገባል ብለዋል።
- ምሁራኖቹ ጨምረው እንደገለጹት የህግ አውጭው አጀንዳዎች (የፖሊሲ ጉዳይ) የህዝብ አጀንዳ እንዲሆን ማህበራዊ ፋይዳው ከፍ ያለ፣ ያልተወሳሰበና ቅድመሁኔታዎች የሌለበት ሊሆን ይገባዋል።

  ለምሳሌ፣ የአልኮል መጠጥ መሸፋፋት ፣ የወሊድ ፈቃድ ማሻሻያ ፣ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ፣

- እነደዚህ አይነት የህግአውጭ አጀንዳዎች በቀላሉ በመገናኛ ብዙሃን ትኩረት የሚስቡና ህዝቡ እነዲደግፋቸው እድል የሚፈጥር ይሆናል።
- አጀንዳው አንድ ጊዜ የህዝቡ ፍላጎት ከቀሰቀሰና የህዝብ ድጋፍ ካገኘ በፖሊሲ አወጣጥ ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ ይቻላል። ለምሳሌ፣ የለማት ድርጅቶች ጠየሚል የመተላለፍ ሁኔታ ፣

# አይነቶች...

2ኛ፣ የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ አመራር /ቀረጻ media agenda setting. የሚዲያ አጀንዳ አመራር ለአጀንዳ አመራሮች አጀንዳ የሚወስነው ማነው ከሚለው ጥያቄ ይነሳል።(who decides the agenda for the agenda-setters? )

- በዜና ዝርዝር ቅደም ተከተል የትኛው መጀመሪያ ፣ የትኛው በሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ተራ መያዝ እንዳለበት የሚወስኑት አርታኢያን ወይም በር ጠባቂዎች ናቸው።
- በር ጠባቂዎች (Gate Keepers ) የመገናኛ ብዙሃን እውቀት ያላቸው አርታኢያን፣ ጋዜጠኞች የህትመት ዋና አዘጋጆች ናቸው። ኤዲቶርያል ስብሰባ ውሳኔ

# አይነቶች.....

- የዜና አርታእያን በሚደያው ላይ የሚወጡትን አንገብጋቢ/አስፈላጊ ጉዳዮች አጀንዳ ለመወሰን የተለያዩ ምንጮችን ይጠቀማሉ።
- የመጀመሪያው ኮሙኒከተሩ/መረጃ አመንጪው የመንግስት አካል የሚሰጣቸው የዜና መግለጫዎች እና የዜና ኮንፈረንሶች ናቸው(Denham, 2010). ለምሳሌ፣ የሰሜን እዝ ጥቃት መግለጫ
- እነዚህ መረጃዎች የህዝብ ጥቅም የተመለከቱ ጉዳዮች ስለሆኑ የበር ጠባቂዎች ዋጋ ይሰጧቸዋል።
- የዜና ምንጭ የሚሆኑ በርካታ መረጃዎች ስለሚያገኙ ከመረጃ እጦት ይላቀቃሉ፡

# አይነቶች...

- በር ጠባቂዎች የሚያዘጋጇቸውን ስራዎች ላይየ ተጽእኖ የሚያሳድረው ሌላው ጉዳይ **የጋዜጠኛው ግላዊ ባህርይ እና የሚከተላቸው ባህላዊ አትኩሮቶች** ናቸው።
- ምሳሌ፣ የማይካድራው ጭፍጨፋ የወንዳጥር መኮንን -አብመድ
- **የጋዜጠኛው ባህርይ ማለትም** ብሄሩ/ዘሩ፣ ጾታ፣ የፖለቲካ ወገንተኝነት በሚዘጋጀው የዜና ጽሁፍ እና የዜናው ማእዘን አቀማመጥ ( angle) ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።
- ጋዜጠኞች የተወለዱበት አገር እና የሚከተሉት ባህል የዜና አዘጋገብ ፣ አጻጻፍ ሁኔታቸው ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ለምሳሌ የዩኤስ ጋዜጠኛ ከአገሩ እሴት ተነስቶ ሊጽፍ ይችላል(ደሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት፣ወዘተ)

# አይነቶች ...

## 3ኛ የህዝብ አጀንዳ አመራር/ቀረጻ(public agenda setting).

- የህዝብ አጀንዳ አመራር ማለት በብዙሃን ተግባቦት ሰራ አማካኝነት ተደራሲያን ወይም ህዝቡ የሚሰጠውን ግበረመልስ ይመለከታል።
- መንግስት አንድ ጊዜ ወስኖ ያወረዳቸው የፖሊሲ ጉዳዮች ዙሪያ ህዝቡ የሚሰጠውን ድጋፍና ተቃውሞ ያካትታል።
  - ለምሳሌ ፣ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ በመንግስት ብቻ የሚቻል አይደለም (ዶ/ር አምባቸው)፣
  - የማህበረሰብ አንቂዎችም በወጣው የመንግስት ውሳኔ ላይ ያላቸውን ግበረ መልስ ይሰጣሉ።

# አይነቶች...

- **ህዝቡ መንግስት ያወጣው ፖሊሲ ህይወቱን በቀጥታ የሚነካ መሆነ ሲረዳና ውሳኔው በደንብ ኮሙኒኬት ከተደረገ በአፈጻጸሙ ላይ በንቃት ይሳተፋል።።**
  ምሳሌ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ፣ የአዲስ አበባ የገበታ ለሃገር ፕሮጄክት
- መገናኛብዙሃን መረጃዎችን በማሰራጨት የህዝብ አጀንዳ እነዲሆን የማድረግ ሚና ይጫወታሉ።

# 3.3. የአጀንዳ አመራር/ቀረጻ ጠቀሜታ እና ጉዳት

- አጀንዳ አመራር የራሱ ጠቀሜታና የጎንዮሽ ጉዳት አለው።
- በአብዛኛው የአጀንዳ አመራር ህዝቡ በአጀንዳው ላይ በቂ መረጃ እንዲኖረው የሚያደርግ ሲሆን ጉዳቱ ተደራሲያን የተወናበደ መረጃ (Biased) እንዲደርሳቸው ሊያደርግ ይችላል።
- የተወናበደ የሚሆንበት አንዱ ምክንያት መገናኛ ብዙሃኑ በራሳቸው መስፈርት ( more vital, based on the prominence of the reports) የህዝብ አጀንዳ ትኩረት እንዳያገኝ ስለሚያደርጉ ነው። ለምሳሌ የጠቅላይ ሚኒስተሩ የኢጋድ ስብሰባ ይልቅ ከሱዳን አዋሳኝ ድንበር ያለው ሁኔታ ህዝቡ መረጃ ሊፈልግ ይችላል።

# IMPACT OF THE MEDIA ON THE PUBLIC POLICY PROCESS 3.4. መገናኛ ብዙሃን በመንግስት ፖሊሲ ሂደት ላይ ያለው ተጽእኖ

- የመጀመሪያው ተጽእኖ መገናኛ ብዙሃን በአንድ ጉዳይ ላይ ተደራሲያኑ ትኩረት እንዲያደርጉ በመምራት ተጽእኖ ማሳረፍ ይችላሉ።
- መገናኛ ብዘሀሀኑ የተመረጠው ጉዳይ ከሁሉም ዘገባዎች በፊት የቅድሚያ ቅድሚያ እነዲያገኝ (prominence )በማድረግ ተደራሲያኑን ወደአንድ አቅጣጫ መምራት ይችላል።
- መገናኛ ብዘሀኑ የራሳቸውን አመለካከትና አተያይ በዘገባው ውስጥ በማካተት ተደራሲያኑ አተያዩን እንዲጋሩና ብሎም የህዝብ አስተያየት ለመገንባት ወይም ተጽእኖ ለማድረግ ይጠቀሙበታል።
-

# የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ተጽኖ ...

- መገናኛ ብዙሀኑ ተደራሲያኑ የሚኖራቸውን ስሜት/ Perception እና ትኩረት ለመሳብ የተለያዩ ቴክኒኮችን ( Attributes) ይጠቀማሉ።
- መገናኛ ብዙሃነ ተደራሲያኑ ላይ ተጽእኖ ለማሳረፍ በቴሌቪዥንና በህትመት የሚጠቀሟቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ።።
- ለምሳሌ በቴሌቪዥን የሚሰራጩ አጀንዳዎችን በተመለከተ ለዘባው የሰጠው የሰአት ርዝማኔ ፣ ጉዳዩ ከሌሎች ዘናዎች/ጉዳዮች ጋር ሲነጻጸር የተሰጠው ቅድሚያ መረዳት የቻላል።
- በጋዜጣ እና በመጽሄት ለጉዳዩ የተሰጠው ቅድሚያ ትኩረት የሚያሳየው ምን ያህል ቦታ ለጉዳዩ እንደተተወ/እንደያዘ እና ጉዳዩ በጋዜጣው ገጽ የትኛው ቦታ ላይ እንደተቀመጠ በማየት መረዳት ይቻላል።

# 3.5. የአጀንዳ አመራር /ቀረጻ አዎንታዊ ፋይዳ

- ሰዎች በየእለቱ መነጋገሪያ የሚያደርጓቸውን ጉዳዮች መገናኛ ብዙሃኑ የሚሰጧቸውን አጀንዳ እንደሆነ፣
- አጀንዳ አመራር/ቀረጻ ንድፈሃሳብ ተደራሲያኑ ተመሳሳይ ጠቃሚ  ጉዳዮች መካከል ቅደም ተከተል በተመሳሳይ መልኩ ማውጣት እንደቻሉ ለመረዳት ያስችላል።
- ተደራሲያን በአንድ አይነት መገናኛ ብዙሃን ለተሰራጩ ጉዳዮች ተመሳሳይ አቋም ሲይዙ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለተላለፉት ጉዳች የተለያየ አቅም መያዝ መቻላቸውን ያስረዳናል።
- የሸማቾች ጥናት ከአጀንዳ አመራር /ቀረጻ አስምህሮ በርካታ ጠቀሜታዎችን ማግኘት የቻለ ሲሆን በተለይም በተተጠቃሚዎች ዘንድ በጣም ተፈላጊ የሆነውን ምርት ለማወቅና በዙያው ልክ መልእክተ ለመቅረጽ የሚያስችል እድል ፈጥሯል።
- ተደራሲያን በጣም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት በመገናኛ ብዙሃን መረጃዎች ላይ ጥገኛ መሆኑና መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት መቻሉ፣

# NEGATIVE EFFECTS OF AGENDA SETTING THEORY

## 3.6. የአጀንዳ ቀረጻ አሉታዊ ተጽእኖ

- መገናኛ ብዙሃን የሚመሯቸው/ የሚቀርጿቸው የመወያያ አጀንዳዎች ከየሚዲያ ማደናገረያ (bias) የጸዱ አለመሆናቸው፣
- ለምሳሌ የክልንተን ለዊኒስኪ ቅሌት ለረዥም ገዚያት የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ ቢሆንም አደናጋሪ መልእክቶች የተካከቱበት በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አለመቻለም፣
- ለረዥም ጊዜ በመገናኛ ብዙሃን ጉዳዩን ማራገብ ሁልጊዜ ጉዳዩ የሞቀ መወያያ ሆኖ እንዲቀጥል የተፈለገ በመሆኑ በተባለት ግለሰቦች ላይ መልካም ያልሆነ ተጽእኖ አስከትሏል፡
- የመገናኛ ብዙሃን ትርፍ ለማግኘት በእርስበእርስ ውድድር ላይ መሆናቸው በየእለዩ የቅሌት ዘገባ ይዘ የመውጣት አባዜ፣
- ተደራሲያኑን በየሰአቱ በመረጃ በማጥለቅለቅ ተደራሲያኑ ጉዳት ላይ እነዲወደቁ አድር ጓል በተለይም በግለሰቦቹ ላይ፣

# CLINTON MONIKA SEX SCANDAL MEDIA AGENDA SETTING

https://www.youtube.com/watch?v=zc7iGSSRKP0

# 3.7. አሉታዊ የአጀንዳ አመራር/ቀረጻ ተጽእኖዎች

- በመገናኛ ብዙሀን የዘወትር አጀንዳ የሆኑ ግለሰቦች፣ በየእለቱ ሰዎች ስለነሱ የሚወያዩ የሚፈርዱ በመሆናቸው ካጋጠማቸው ችግሮች ለመላቀቅ በጣም ይቸገራሉ፣
- አልፎ አልፎ ህጻናት በአማጽያን ወይም ተቀናቃኝ ጦር መታገታቸውን አጀንዳ ማደረግ አሉታዊ ተጽእኖ በቤተሰብ እና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርስ መሆኑ፣
  - ምሳሌ፣ በሰሜን እዝ ከሰራዊቱ ጋር የዘመተ ህጻን ልጅ፣
- በመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች እና በፖለቲከኞች መካከል የጥቅም ትስስር ካለ በመገናኛ ብዙሃን የሚሰራጨው መልእክት /መረጃ ሁሉ የፖለቲካ ተጽእኖ የሚያርፈበት መሆኑ ሌላው ተጽእኖ ነው፣

# 3.8. አጀንዳ አመራር/ቀረጻ/አጀንዳ ግንባታ /አጀንዳ AGENDA SETTING VS AGENDA BUILDING VS AGENDA MELDING

- **አጀንዳ ግንባታ  አጀንዳ አመራር ወይም ቀረጻን የመረጃ ስረመሰረት ሲፈትሹ የተፈጠረ ነው።**
- **መልእክቶቹ የተገነቡበት መንገድ፣ አጀንዳ አመራሩ /ቀረጻው ምንጭ ሲጠና በመገናኛ ብዙሃን እንደተፈጠረ  ፍንጭ ቢያገኙም ሙሉበሙሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዳልሆነ አረጋገጡ።**
- **ይልቁንም ተጨማሪም ምርምር ማድረግ ጀመሩ፣ በጉዳዩ ማፍለቅ ላይ የተሳተፉ ሰዎችን ማናገር፣ ሪፖርቶቹን መዳሰስ፣ ቃለመጠይቅ ማድረግ ጀመሩ።.**
- በዚህም መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት መልእክቶቹ ከመታተማቸው በፊት በፖሊሲ አመንጪዎች፣ በህዝቡ፣ እና በመገናኛ ብዙሃን ቅንጅት ቁልፍና አንገብጋቢ ጉዳዮችን መለየት ችለዋል።።
- ተመራማሪዎቹ በጥናታቸው መደምደሚያ አጀንዳ ግንባታ ሃሳብ ማመንጨት ቻሉ።
- በአጀንዳ ግንባታ ወቅት ከመገናኛ ብዙሃን ከሚያመጡት ተጽእኖ ይልቅ የመልእክቶቹ ቀረጸ ይበልጥ ትክረት የሚሰጥ ነው።

# 3.9. አጀንዳ ቀረጻ ከሌሎች የአጀንዳ ግንባታና አጀንዳ ውሀደት ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት

- ሮጀርስ እና ዴሪንግ (Rogers and Dearing (1988)በሶስቱ የአጀንዳ አመራር ባህርያት አንድነትና ልዩነት ዙሪያ ሃሳብ ሰንዝረዋል።
- **አጀንዳ አመራር /ቀረጻ** የመገናኛ ብዙሃኑን አጀንዳ ወደህዝቡ ማሸጋገር ነው‘setting’ refers to transferring the media agenda onto society and the public agenda.
- **አጀንዳ ግንባታ** መገናኛ ብዙሃን እና ህዝቡ የመንግስትን ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ በጋራ የሚያሳድሩበት ሁኔታ ነው ‘
- በዚህም በመገናኛ ብዙሃን፣ በህዝቡ እና በፖሊሲ አውጭዎች መካከል እርስበእርስ ግንኙነትና መመጋገብ ይስተዋላል።
- በቅርቡ ምሁራኑ እንዳረጋገጡት ጋዜጠኞች(ሚዲያው) አጀንዳ በመቅረጽ ተሳትፎ የሌለውና ይልቅንም የህዝብ ተቋማት ያወጡትን አጀንዳ የማስተላለፍ ሚና ብቻ እየያዘ እንደመጣ ነው።

# ክፍል አራት፣

## የአጀንዳ አመራር፣ ግንባታና አንለይን አጀንዳ ቀረጻ ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ

# የአጀንዳ አመራር፣ ግንባታና ኦንላይን አጀንዳ ቀረጻ ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ

- መገናኛ ብዙሃን አጀንዳ የመቅረጽ መብት እንዳላቸው በብዘሃን መገናኛ እና መረጃ ነጻነት አዋጅ 590/2000 አንቀጽ 3 በግልጽ ደንግጓል።
- አገራችን የመገናኛ ብዙሃን እየተስፋፉ የሚገኝባት በመሆኑ  መደበኛ የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ አመራር/ቀረጻ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማበረታታት ያስፈልጋል።
- በመደበኛ መገናኛ ብዙሃን ሁሉንም ክልልች በአብዛኛው የሰላም እሴት ግንባታ፣  የግጭት ምንጮችን ማድረቅ፣ የልማት ጉዳይ፣ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ጉዳዮችን አተኩሮ በየጊዜው መልእክት ቀርጸው ማሰራጨት ይገባቸዋል።።
- የመንግስት አካላት በየደረጃው ፣ ከፌዴራል እስከ ክልልልና ወረዳ በጉያቸው የያዙትን መረጃ  በቋሚነትና በተከታተይ በኮሙኒኬተሮች እና በበላይ አመራሩ አማካኝነት ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ መስጠት ይገባቸዋል። በዚህም መገናኛ ብዙሃን በቂ መረጃ እንዲኖራቸውና አጀንዳ ቀርጸው ለማስተላለፍ የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል።

# ለኮሙዩኒኬሽን ያለው ፋይዳ

- የኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 በተለይ አጀንዳ ስለመቅረጽ፣ የመነግስት መረጃ ለዜጎች(መገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ) ክፍት ሊሆን ስለሚገባው ይደነግጋል።
- 3) Freedom of the press and other mass media and freedom of artistic creativity is guaranteed. Freedom of the press shall specifically include the following elements:

(a) Prohibition of any form of censorship.
(b) Access to information of public interest.

(4) In the interest of the free flow of information, ideas and opinions which are essential to the functioning of a democratic order, the press shall, as an institution, enjoy legal protection to ensure its operational independence and its capacity to entertain diverse opinions.

# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...

xNq{ 4mgÂ¾ Bz#¦N nÉ SImçÂcW

1. ymgÂ¾ Bz#¦N nÉnT b?g mNG|t :WQÂ xG"aLÝÝ

QDm MRm‰ b¥N¾WM mLk# ytklkl nWÝÝ

2. bmgÂ¾ Bz#¦N nÉnT §Y gdïC y¸ÈI#T ?g mNGSt$N m\rT b¥ DrG b¸w-# ? ¯C BÒ YçÂLÝÝ

3. ¥N¾cWM ymNGST xµ¸ymgÂ¾ Bz¦N ¥Hb‰êE tGÆ‰cWN lmw ÈT”- h¼ z@Â ወይም መረጃን የመቀበል እና የማሰራጨት


◌I¼ bL† L† g#Ä× ×C §Y xStÃyT wYM TCT y¥QrB½ wYM

/¼ ytlÃ† l@lÖC zÁãCN bm-qM y?ZBN xStÃyT bmQr{ £dT ymútF# mB¬cWN ¥KbR YñRÏ℗¸”


# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...

- ኮሙኒኬሩ  አጀንዳ ለመምራት/ ለመቅረጽ በሚያስብብት ወቅት  የማህበራዊ ሚዲያ ፋይዳ ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ አለበት።
- በ 2010  የአረብ ጸደይ አብዮት Arab Spring, ሞሃመድ ቡአዚዝ የተባለ ወጣት ነጋዴ ራሱን በእሳት አቃጥሎ መሞቱ  ፣ በግብጽ ወጣቶች በተቃውሞ ጣህሪር አደባባይ እንዲወጡ ዩቱብ፣ ትዊተር ወደአደባባይ እነዲወጣ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።
- በኢትዮጵያ ከ2008 ጀምሮ የተቀጣጠለው የህዝባዊ እምቢተኝነት በፌስቡክ መረጃ በመለዋወጥ በአካል የሚደረገውን ተቃውሞ አግዟል።
- በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የማህበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች ፋስቡክ፣ ዩቱብ፣ ትዊተር፣ወዘተ ዋነኞቹ ናቸው።


# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...




# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...



# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...




# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...




# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...



# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...



# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...



JAN 2019


## TOP GOOGLE SEARCH QUERIES IN 2018

BASED ON SEARCHES THROUGHOUT 2018


| # | SEARCH QUERY | INDEX |
|---|---|---|
| 01 | ETHIOPIA | 100 |
| 02 | FACEBOOK | 97 |
| 03 | NEWS | 95 |
| 04 | VIDEO | 84 |
| 05 | YOUTUBE | 47 |
| 06 | FB | 47 |
| 07 | WWW | 41 |
| 08 | GOOGLE | 38 |
| 09 | GMAIL | 38 |
| 10 | MUSIC | 33 |

| # | SEARCH QUERY | INDEX |
|---|---|---|
| 11 | SPORT | 31 |
| 12 | BBC | 27 |
| 13 | AMHARIC NEWS | 21 |
| 14 | FACEBOOK LOG IN | 21 |
| 15 | ARSENAL | 20 |
| 16 | ESAT | 19 |
| 17 | FILM | 18 |
| 18 | PREMIER LEAGUE | 17 |
| 19 | NEAEA | 17 |
| 20 | WWW.NEAEA.GOV.ET | 16 |


# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...




# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...



# ለኮሙኒኬሽን ስራችን ያለው ፋይዳ...



# ለኮሙኒኬሽን ሰራችን ያለው ፋይዳ...



JAN 2019

## TOP YOUTUBE SEARCH QUERIES IN 2018

BASED ON SEARCHES ON THE YOUTUBE PLATFORM THROUGHOUT 2018

| # | SEARCH QUERY | INDEX |
|---|---|---|
| 01 | MUSIC | 100 |
| 02 | NEW MUSIC | 40 |
| 03 | NEWS | 38 |
| 04 | MUSIC 2018 | 32 |
| 05 | ETHIOPIAN MUSIC | 31 |
| 06 | ETHIOPIA | 25 |
| 07 | MOVIES | 25 |
| 08 | MEZMUR | 25 |
| 09 | NEW MUSIC 2018 | 21 |
| 10 | FILM | 21 |

| # | SEARCH QUERY | INDEX |
|---|---|---|
| 11 | ESAT | 20 |
| 12 | AMHARIC MUSIC | 15 |
| 13 | NEW ETHIOPIAN MUSIC | 15 |
| 14 | ETHIOPIAN MUSIC 2018 | 12 |
| 15 | COMEDY | 12 |
| 16 | ETHIOPIAN MOVIE | 12 |
| 17 | ABIY | 11 |
| 18 | ESAT NEWS | 11 |
| 19 | KANA | 10 |
| 20 | ZEMEN | 10 |

34

SOURCE: GOOGLE TRENDS (ACCESSED JANUARY 2019); KEPIOS ANALYSIS. NOTES: GOOGLE DOES NOT PUBLISH SEARCH VOLUMES, BUT THE 'INDEX' COLUMN SHOWS RELATIVE VOLUMES FOR EACH QUERY COMPARED TO SEARCH VOLUMES FOR THE TOP QUERY (AN INDEX OF 50 MEANS THAT THE QUERY RECEIVED 50% OF THE SEARCH VOLUME OF THE TOP QUERY).

Hootsuite we are social

# FAKE AND DISINFORMATION

Ethiopian News liked

**Martin Plaut** @martinplaut · 2h

We cannot allow Ethiopia to become this generation's Rwanda



We cannot allow Ethiopia to become this generation'...
Source: Dallas Morning News OPINION We cannot
this generation's Rwanda ...

**Neamin Zeleke** @NeaminZeleke · 27m

Is #EU interested in a destabilized #Ethiopia&region? Why undermine, when #UN & Govt delivered food&medicine to #Tigray @Ethiopianairlines flying, utility services resorted #MekeleUniversity held graduation, provisional admin started? @EUSR_Rondos @EUinEthiopia @JanezLenarcic

**Janez Lenarčič** @JanezLenarcic · Dec 19

‼ Ethiopia's #Tigray is on the edge of a humanitarian catastrophe risking destabilisation of the wider region.

To address the humanitarian crisis, the EU is increasing its emergency funding for the area, including #Sudan and #Kenya, by €23.7 million.



Ethiopian News liked

**Martin Plaut** @mart

Ethiopia's prime mini
reformer and a peace
has launched a major
threatens the stability



**e Associated Press** @AP · Nov 30

e fugitive leader of **Ethiopia**'s defiant Tigray region is calling on Prime inister Abiy Ahmed to "stop the madness" and withdraw troops from the gion as he asserted that fighting continues "on every front" despite Abiy's aim of victory.



'Stop the madness,' Tigray leader urges Ethiopia's PM
NAIROBI, Kenya (AP) — The fugitive leader of Ethiopia's defiant Tigray region on Monday called on Prime Minister Abiy Ahmed to "stop the ...
apnews.com

# FAKE AND DISINFORMATION

**Al Mariam** @AlMariam1 · Dec 17

EUROPEAN UNION: TAKE YOUR AID AND SHOVE IT!

almariam.com/2020/12/02/u-s...

@AbiyAhmedAli, @fitsumaregaa, @SahleWorkZewde, @MoP_Ethiopia, @demekeMek11, @MoP_Ethiopia, @NeaminZeleke



EU suspends nearly €90M in aid to Ethiopia over internal con
The bloc wants Ethiopia's government to cease hostilities an
humanitarian access to the Tigray region.
politico.eu

**Al Mariam** @AlMariam1 · Dec 18

1/2 -- Allegation Norwegian TPLF apologist Kjetil Tronvoll raped a "16 year old minor" promising migration to Europe & now pregnant is deeply disturbing. Tronvoll's announcement after allegation that, "I am taking a break from twitter" is even more disturbing.

> **Kjetil Tronvoll** @KjetilTronvoll · Dec 17
> To all followers and friends: I am taking a break from twitter, as the slur campaign against me by certain Ethiopian and Eritrean trolls is spinning out of propotions. Also z serious & totally unfounded accusations levelled by Ethi authorities r becoming increasingly concerning.



# FAKE AND DISINFORMATION




On December 9, 2020, the New York Times published a story written by Abdi Latif Dahir under the headline, "Fleeing Ethiopians Tell of Ethnic Massacres in Tigray War".

Here are a few excerpts from the *lie-filled story* of Abdi Latif Dahir the "Tigray War" anchored in the personal account of alleged victim "Ashenafi Hailu":

> *...Mr. Ashenafi and dozens of other Tigrayan refugees fled the violence and settled outside the remote and dusty town of Hamdayet, a community of just a few thousand people near the border, where I spoke to them. Their firsthand accounts, shared a month after Ethiopia's prime minister, Abiy Ahmed, declared war on the Tigray region, detail a devastating conflict that has become a grisly wellspring of looting, ethnic antagonism and killings...*
>
> *...Mr. Ashenafi, 24, was racing on his motorcycle to the aid of a childhood friend trapped by the Ethiopian government's military offensive in the northern region of Tigray when a group of men on foot confronted him. They identified themselves as militia members of a rival ethnic group, he said, and they took his cash and began beating him, laughing ominously.*
>
> *"Finish him!" Mr. Ashenafi remembered one of the men saying.*
>
> *...As they tightened the noose around his neck and began pulling him along the road, Mr. Ashenafi was sure he was going to die, and he eventually passed out. But he said he awoke alone near a pile of bodies, children among them. His motorcycle was gone...*
>
> *... As the fighting in Tigray continues, it is degenerating into a guerrilla war that could unravel both Ethiopia's national fabric and the stability of the entire Horn of Africa region...*
>
> *... After Mr. Ashenafi awoke and saw the bodies around him, he trudged through a nearby forest to reach the home of his friend, Haftamu Berhanu, who took him in. Photos taken by*

# 5. ማጠቃለያ

- የአጀንዳ አመራር/ቀረጻ በመገናኛ ብዙሃን፣ በመንግስት እና በራሱ በህዝቡ ሊነሳ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል
- አጀንዳ ቀረጻ ከይዘት ትንተና እና ከህዝብ አስተያየት ውጤቶች መነሻ ሊዘጋጅ ይችላል
- ከሙኒኬተሮች የሚያዘጋጇቸው መልእክቶች የተደራሲያንን ልምድ፣ ባህል፣ የትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ ሁኔታ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል
- ከሙኒከተሮች በቋሚነት እና በየወቅቱ ለመገናኛ ብዙሃን በፕሬስ መግለጫ እና በፕሬስ ኮንፈረንስ መረጃ መስጠት፣ ተቋሙ የያዛቸውን ቁልፍና አንገብጋቢ ጉዳዮች ለይቶ በማሰራጨት የደንበኞቹን/የተጠቃሚዎቹ አመለካከትና ሃሳብ ላይ ተጽእኖ ማሳደር ይችላሉ፣
- ከመደበኛውና ልማዳዊው መገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ቴሌግራም፣ ዩቱብ  ተቋሙን ስራዎች ለመላ አለም አድማጭ ተመልካቾች ማቅረብ የወቅት ጥያቄ ነው።

# BROWSE

- Ahramonline.com
- AP  (associated Press)
- BBC Amharic
- DW Amharic
- New York Times
- Sudan Tribune

# አመሰግናለሁ!